እንደትላልቅ ሕፃናት ...

አላህ ለሠዉ አዛኝ የሆነ ጌታ ነው፡፡ አዛኞችን ይወዳል፡፡ ለአዛኞችም ያገናል፡፡ እዝነትን የሚወድ ጌታ አርስበርስ ተዛዘኑ አለን፡፡ አዛኝ መሆን የአላሀን የእዝነት ባህሪ መውረስ ነው፡፡ በርግጥም ጥሩ ሙአሚን ለስላሳ ነው፣ አሩህሩህ ነው፡፡ ምድር ላይ እየኖርን ያለነው በአላህ እዝነት ነው፡፡ ወጥተን የምንገባዉም በረሕመቱ ነው፡፡

ብዙዎቻችን ልጅ አያለን አዛኝ ነበርን፡፡ ልበ ሩህሩህ፡፡ በተለያየ ነገሮች ያልተበከልን ልበ ንዑሕ ስለሆንን ይመስለኛል፡፡ አያደግን ስንሄድ ግን አየጠጠርን፣ አየደያርን፣ አየጨከንን መጣን፡፡ የምናየው የምንሰማው ሁሉ አደነደነን፡፡ ያንን የልጅነት ቀልባችንን ይዘን አድገን ቢሆን ኖሮ እንዴት መልካም በሆነ፡፡

ከሰዎች ሁሉ ቆንጆዎቹ ትላልቅ ሕፃናት ናቸው ይባላል፡፡ ትላልቅ ሕፃናት በዕድሜ ትልቅ ናቸው፡፡ አርጅተዋል፣ ሸብተዋል፡፡ ግና የቀልባቸው ሁኔታ ገና እንደ አምስት ዓመት ሕፃን ነው፡፡ ለሰው ያገናሉ፣ ስለሰው ይጨነቃሉ፡፡ ከልጅ አሰከ አዋቂ የማያገኑለት የሕብረተሰብ ከፍል አንድም የለም፡፡ ኑሯቸው ገቅተኛ የሆነ የጎረቤት ልጆች ሁኔታ ያሳስባቸዋል፡፡ መንገድ ላይ እጅ የሚዘረጋላቸው ለማኞች ሁኔታ ያሳዝናቸዋል፡፡ የአልጋ ቁራኛ የሆነ ሀመምተኛ ሁኔታ ልባቸዉን ይነካል፡፡ በረንዳ ላይ ያየዋቸው ልጆች ሁኔታ ለቀናት እንቅልፍ ያሳድራቸዋል፡፡ የተራበ ሰው ያየ ቀን ምግብ አይበላቸዉም፡፡ የተቸገረ ባጋጠማቸው ጊዜ መኖር ትርጉም አይሠጣቸዉም፡፡ የታረዘ ሲመለከቱ መልበስ አይጥማቸዉም፡፡

አዛኞች እናት አባታቸዉን ለምን ለለማኝ አትሠጡም ብለው እንደሚያስጨንቁ ሕፃናት ናቸው፡፡ ችግረኛን አይተው ማለፍ አይሆንላቸዉም፡፡ ከእዝነት አንፃር እንደ ሕፃናት እንሁን፡፡ መስጠት፣ ማዘን፣ መርዳት፣ ማገዝ .. ባህርያችን ይሁን፡፡ ሰው ሁሉ ጨካኝ ቢሆን እንኳ ጭካኔን አንለምድ፡፡ ሰዎች በከለከሉ ጊዜ እንሰጥ፤ ሰዎች በጨከነበት ዘመን እንዘን፣ ሰዎች ሰው በገፉበት ጊዜ እናስጠጋ፡፡ የሰው ሁኔታ የሚሰማን ከሆነ ያኔ ሰው ነን፡፡ ካልሆነ ከግዑዝ በምን እንለያለን፡፡

እዝነት በመጥፋቱ እና ሰው ሁሉ ራስ ወዳድ በመሆኑ ምክንያት ዓለም ላይ ሞት በዛ፡፡ ችግር በዛ፣ ርሃብ በዛ፣ ስደት በዛ፣ ጦርነት በዛ፡፡ ብንተዛዘን ኖሮ ምድር ላይ ችግር ባልኖረ፣ ስደትና ጦርነትም ባልተከሠተ ነበር፡፡ አላህ ሆይ ለባሮችህ አዛኝ የሆነች ቀልብ ስጠን፡፡ ከጨካኞችም አታድርገን፡፡

የመዘግየት ቅጣት

ኢብኑ ሰዕድ ጠቢታት በተሠኘው መጽሐፋቸው ዉስጥ እንዳወሩት ሶናቢሒ የሚባል ሰው እንዲህ ይላል፡- " ነቢዩ ሶ.ዐ.ወ ዘንድ በስያት ለማረፍ አሰበን ከየመን ተንቀሳቀስን፡፡ መዲና ዳር፟ ስ በደረስን ጊዜ አንድ ፈረሠኛ ሰው መጣና " ነቢዩን ሶ.ዐ.ወ. ከአምስት ቀናት በፊት ቀበርን አኮ፡፡" አለን፡፡

የአምስት ቀን ወደኋላ መዘግየት ሶናቢሒ የነቢዩን ሰ.ዐ.ወ. ፊት እንዳያይ አደረገው፡፡ ዮን የሚያበራ እና ሰው ሁሉ ለማየት የሚመኘዉን ፊት፡፡ ነቢዩን ሶ.ዐ.ወ. ማየት መታደል ነው፡፡ ቢያገኛቸዉና ቢያያቸው ኖሮ ደስታው ምን ያህል ሊበዛ እንደሚችል አስቲ አስበት፡፡ በርግጥ ቢያያቸው ኖሮ ሶሐባ ሊባል የሚ፟ችል ሥም ሊያገኝ የሚችለው ሰዉዬ ወዲያው ወደ ታቢዒይነት ደረጃ ወረደ፡፡ እርሣቸዉን ባለማግኘቱ እንኳን እሱ ታሪኩን የሰማዉም ሰው ሁሉ ይቆጭበታል፡፡ አለመታደል፡፡

የሶናሒቢ ታሪክ አንድ ነገር ያስተምረናል፡፡ ኸይር ነገር ለመሥራት ዛሬ ነገ እያልን ማዘግየት እንደሌለብን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቶሎ ባለመወሰናችን ብቻ የሶናሒቢን ዓይነት ከባድ ቅጣት እንቀጣለን፡፡ ለሶናቢሒ የደረሰው እጣ ይደርሰናል፡፡ ለኸይር ነገር ካልፈጠንን፤ ቆይ ዛሬ ነገ እያልን የምንቀጥር ከሆነ፣ ልንጠይቀው የነበረ አስረኛ ይፈታና እናፍራለን፡፡ ልንሰበኘው የነበረ በሽተኛ ይሞትና እንፀፀታለን፡፡ ከዚህ ቀደም ቀን እየቀጠርንና ጊዜ እየነተትን ስንትና ስንት መልካም ነገሮች አልፈዉናል፡፡

ወዳጄ! ዉጤት ለሚያስገኝልህ ሥራ አትቅጠር ፍጠን፡፡ ብረትህን ጊዜው ሳይረፍድ በትኩሱ ቀጥቅጠው፤ ካልሆነ የምትፈልገዉን ቅርጽ አይዝልህም፡፡ ልጅህን በትንሽነቱ ቆንጥጠው ከፍ ካለ ይደርቃል አይስተካከልልህም፡፡ በተባለው ጊዜ ባለማመልከትህ ስንት የምትፈልገው ሥራ አለፈህ፡፡ በመዘግየትህ ምክንያት ስንት የምትጓጓለት ሐጃ አመለጠህ፡፡ በርግጥ ሁሉ ነገር በቀ፟ ቀደር ነው፡፡ የምታገኘዉም አላህ የወሰነልህን ብቻ ነው፡፡ ግና እሱ የፃፈልኝ አይቀርም ብለህ እጅህን አጣጥፈህ አትቀመጥ፡፡ ለመልካም ነገር መቅደምን፣ ቶሎ መነሳትን፣ ለበጎ ነገር መታተርን ባህሪህ አድርግ፡፡ ኸይር ነገርን ዛሬ ነገ ብለህ አታዘግይ፡፡ አሁኑኑ ሥራው፡፡

የታመመን ለመጠየቅ፣ ዑለማን ለመዘየር፣ አስረኛ ዘንድ ለመድረስ፣ ዘመድን ለመጎብኘት አመቺ ጊዜ አትጠብቅ፡፡ ካሁን በላይ አመቺ ጊዜ የለምና፡፡ ከዘገየህ፣ ከቆየህ ብዙ የሚያመልጥህ ነገር ይኖራል፡፡ እንደ ሶናቢሒ ቁጭትህ ይበዛል፡፡

እያረፍን እንቀጥላለን ...

ኢስቲግፋር - ለቀልብህ ዕረፍት፣ ለአዕምሮህ እርካታ፣ ለነፍስህ ደስታ፣ ለልቦናህ ጤና፣ ለገንዘብህ በረከት፣ ለመንፈስህ ምግብ ነው።

ኢስቲግፋር ... ራስህን ታድስበታለህ፣ ጉዳይህን ትፈጽምበታለህ፣ በተሰብሆን ታስተካከልበታለህ፣ ኑሮህን ታስዉበበታለህ፣ ሪዝቅህን ታሰፋበታለህ፣ ኃጢአትሆን ታረገፍበታለህ፣ ሀሳብ ጭንቀትን ታባርርበታለህ። በምንም ዉስጥ ሁን፣ ኢስቲግፋርን አዘውትር።

****

ሕይወት ዋጋዋ ዉድ ነው፣ ዕድሜ በገንዘብ አይተመንም፣ አስትንፋሳችን ርካሽ አይደለም፣ አላህ ምድር ላይ ያስገኘን ለተራ ጉዳይ አይደለም፣ ያልሆኑ ሪሌሽኖችን ጨከናችሁ አቁሙ፣ በሞቱ ሀልሞች ላይ መሠረታችሁን አትገንቡ፣ የማይረቡ ጓደኝነቶችን ቁረጡ፣ በተራ ፊልሞችና መጽሐፎች ጊዜያችሁን አታቃጥሉ፣ ከማይመጥኗችሁ ሰዎች ጋር አትዋሉ፣ ቁምነገር በማይገኝባቸው ቦታዎች ላይ አትገኙ። አነኚህ ነገሮች ሁሉ ከዕድሜያችሁ ይቆርጣሉ፣ ከሕይወታችሁ ይቀንሳሉ። መኖራችሁ ካልቀረ ኮስተር በሉ። እውነተኛ ሕይወት ኑሩ፣ በፍቅር የተሞላ፣ በቁምነገር የታጀበ፣ በዉጤት የሰመረ ሕይወት።

****

አትስማችው ....

በ2019 በሥነጽሑፍ የኖቤል ተሸላሚ የነበረችው ቶኒ ሞሪሰን የምትባል ሴት ሞተች። ለሽልማቱ ብቸኛ ጥቁር ሴት ነበረች። በልጅነቷ መጽሐፍ ማንበብ እጅግ ትወድ ነበር። : አናቷ ትወቅሳታለች። "ልጄ ሆይ ተኚ፤ አንቺ ትልቅ ቦታ ታሲብያለሽ፤ እነርሱ ግን ለጥቁር ቦታ የላቸዉም።" ትላት ነበር።

በዚህ መልኩ ብዙዎች ተስፋ ተስፋ የሚያስቆርጥ ንግግር ይናገሩሃል። አንዳንዱ ያሳለቅብሃል። ሌላው ፊጽ አትደርስም አይሳካልህም ይልሃል። ሌላው ወይ ለልፋትህ ይፈራልሃል ወይ ደግሞ ያንተኑ አቅም ይጠራጠራል ። ግና አንተ የጀመርከዉን በርታና ጨርስ፤ በራስህ ተማመንና ጉዞህን ተጓዝ። ህልምህንና ዉስጣዊ ዝንባሌህን ተከተል። በራስ ከተማመንክ የትኛዉንም ከባድ ዳገት ትወጣለህ።

ዉለታን አለመርሳት ...

የሰው ዉለታ ከብዷችሁ ያውቃል? አላስቀምጥ አላስኬድ አላስተኛ ያላችሁ የሰው ዉለታስ ይኖር ይሆን? የሱንስ ዉለታ አላህ አንጂ አኔስ ችዬ አልመልሰዉም ብላችሁ ከራሣችሁ ጋር አዉርታችሁ ይሆን!!

እንኳን እኔና አናንተ ነቢያችንም (ሶ.ዐ.ወ.) ቢሆኑ ምድርን ሲሰናበቱ አቡበከር ለርሣቸዉና ለዲኑ የዋሉት ዉለታ ያሳስባቸው እንደነበር ግልጽ ነው "የሁሉንም ሰው ዉለታ መልሰናል የአቡበከር ሲቀር::" ነበር ያሉት ምድርን ሲሰናበቱ አካባቢ::

መ·አሚን የሰዉን ዉለታ የሚረሳ አይደለም:: የአምላኩን፣ የነቢዩን፣ ወላጆቹን፣ የቤተሰቦቹን፣ የባለቤቱን፣ የአኺራ ወንድም አህቶቹን መልካምነትም አይዘነጋም:: ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ.) "መልካም የዋለላችሁን ሰው ካሰት:: መካስ ካልቻላችሁ ዱዓ አድርጉለት::" ያሉት::

ዉለታ ገንዘብ ብቻ አይደለም:: ሰዎች ለኛ የዋሉት መልካምነትም ጭምር ዕዳችን ነው:: በተቻለ ሁሉ መረሳት የለበትም:: ስንደከም መልካም ቃላት ያዋሱን፣ ገንዘብ ያበደሩን፣ አጅ ሲያጥረን ያሳከሙን፣ ጉዳያችንን ሳንነግራቸው ምን ልርዳህ ምን ጎድሎሃል ... ብለው የጠየቁን፣ ደስታችን ብቻ የሚያስደስታቸው፣ ማግኘታችን የሚያስፈነድቃቸው፣ በሰው መሀል ደምቀን መታየታችን የሚያኮራቸው፣ የምን ላድርግለት ምን ልሁልነት ሀሳብ የሚሰጨንቃቸው፣ እነኚህ ሁሉ ከቻልን ጀዛቸዉን ለመክፈል ጊዜና አጋጣሚ የምንጠብቅላቸው ባለዉለታዎቻችን ናቸው::

በዚህች ምድር ላይ ስንኖር በሰው መካከል ቆመን እንድንሄድ ምክንያት የሆኑን፣ ስንወድቅ ያነሱን፣ ተስፋ ስንቆርጥ አይዞህ ያሉን፣ ስንደከም ያበረቱን፣ በሀሳብም ሆነ በገንዘብ የረዱን ይኖራሉ:: ከራሣው በላይ የኛ ጉዳይ አብዝቶ የሚያሳስባቸው አንዳንድ አላህ በእዝነቱ ለኛ ብቻ የመደበልን የሚመስሉ እኛን መኻደም ሀሴት የሚያጎናፅፋቸው ሰዎች አሉ:: እንደ ነዳጅ ሆነው ጠቅመዉናል፤ ስንደከም ኃይል ሆነዉናል፣ ሰንቆም ገፍተዉናል፣ ስንረሳ አስታዉሰዉናል፣ ስንጠፋ ጠይቀዉናል፣ ስንታመም ዘይረዉናል:: እጃችን ባጠረ ጊዜ ለነኚህ ሰዎች ልናደርግላቸው የምንችለው ትልቁ ነገር ዱዓ ነው::

ዉለታቸው በዝቶብን ጀርባችን ላጎበጠን ወንድም እህቶች ሁሉ አላህ ከምንለው በላይ በመልካም ይመንዳቸው:: ጀዛኩሙሏሁ ኸይራ::

ነሕኑ ቀሰምና በይነሁም መሚሸተሁም ...

በኛ እሩቱ ዓለም ብዙን ጊዜ ታደላለች። ሰለማዳላቲ ምድር ላይ በተፈጠባማሁ የምኖየው ነው። አላህ ግን ፍትሃዊ አምላከ ነው አያደላም። አያዳላም። ግና የሚያዩት ነገሮች ደስ ላይሏችው ሊቀሩ ለምን ብለው የሚጠይቁ ብዙ ናቸው። መልካሞች ሰፈተን መጥፎዎች ፈታ ብለው ሲኖሩ እናያለን። ተንኮለኛ ሰው ሰደነቅ፣ ወራዳ ሰው ሲከበር፣ ከፉ ሰው ሲወደስ፣ ግፈኛ ሰው መንገድ ሲለፋቅለት፣ ሌባ ሰው ቦታ ሲሠጠው ያጋጥማችኋል። ቅንና ልበ ንፁህ ስትሆኑ በዚህ የዓለም ሁኔታ ለምን እንዲህ ሆነ ማለታችሁ አይቀርም። ትከፋላችሁ። ሆድ ይብሳችኋል።

ወዳጆቼ ... ዱንያ የሚገባዉን ትታ ለማይገባው ስትሸልም፣ መከበር ያለበትን አዉርዳ የሌለበትን ስታነሳ አይግረማችሁ። ይህን ሁሉ የሚያደርገው የፈጠረን ጌታ አላህ ነዉና ብዙም አይግረማችሁ። እሱ ነገሮችን የሚያደርገው በዕውቀት እና በጥበቡ ነው። እኛ የነገሮችን ላያቸዉንና ጊዜያዊ ሁኔታቸዉን ስናይ እርሱ ደግሞ ዉስጣቸዉንና መጨረሻቸዉን ያውቃል። ስለሆነም እሱ በሚሠራቸው ነገሮች ማጉረምረምና መነጫነጭ አይገባም። በሥራዬ ምን ያገባችኋል የሚል በሚመስል መልኩ "እኔ ነኝ ሲሳያችሁንና ኑሯችሁን የከፋፈልኩት።" ብሎ ነግሮናል በቁርአኑ።

አሁን ያለንበት የወጣትነት ወይም የጎልማሳነት ዕድሜ ላይ ቆመን ከታች ጀምሮ ያለዉን ሕይወታችንን ብንቃኝ ብዙ እንታዘባለን። በአንድ ከፍል ተምራችሁ የት ይደርሱ ይሆን የተባሉ ጎበዞች ተሰናክለው አላጋጭ ሰነፎች ትልቅ ቦታ ላይ ደርሰው ትመለከታላችሁ። የምታዩት ሁሉ የሆነው በአላህ ፈቃድ ነው። ለዚህ ሠጥቶ ለዚያ የከለከለው፣ ይህን ከፍ አድርጎ ያን ያቀለለው፣ አንዱን ዝነኛ አድርጎ አንዱን ከዐይን የሰወረው አላህ ነው። ያንዱን ጉዳይ አፍጥኖ ያንዱን ያዘገየው፣ ላንዱ ልጅ ሠጥቶ ለሌላው የከለከለው፣ ለሌላው ሀብት አትረፍርፎ ሌላዉን ያደኸየው፣ ላንዱ ነስቶ አንዱን ያንበሸበሸው አላህ ነው። እሱም ይህን ያደረገው ጥሩዎችን ሊበድል፣ መጥፎዎችን ሊጠቅም ብሎ አይደለም። ፍትሃዊ አምላካችን ከዚህ የጠራ ነው ሱብሐነላህ። ወዳጆቼ መልካሞቼ ናቸው።

ወዳጆቼ! የምድር ላይ ስጦታዎችን የከፋፈለው አላህ ነው። ስለሆነም ግራ ቀኝ ዐይንህን ወዲህ ወዲያ አትወርዉር። ወደላይ እያየህ አትጎምጅ። እሱ ከኔ እንዴት ይበልጣል ብለህ አትብከንከን። በተሠጠህ ነገር እርካ፣ ያለህን ነገር ዉደድ። አላህ ለሌሎች በሠጠው ነገር አትቅና፣ አትመቅኝ።

ለቀልብዎ ርጥበት

ከኡሳማ ኢብኑ ዘይድ እና አቢ ሁረይራ (ረ.ዐ.) እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ. እንዲህ አሉ፡-

"የቂያማ ቀን ከሰው ሁሉ ወደ ኃያሉና የተከበረው አላህ ይበልጥ ቅርብ የሚሆኑት ዱንያ ላይ እያለ ርሃቡ፣ ጥሙና ሐዘኑ የረዘመባቸው፣ ባዶ እግራቸዉን የሚሄዱ፣ አላህን የሚፈሩ፣ የሆነ ቦታ ላይ ቢገኙ የማይታወቁ፣ ቢቀሩም ሰው የት ጠፉ ብሎ የማይጠይቃቸው፣ ግና መሬት ሁሉ የምታውቃቸው፣ መላእክት የሚከቧቸው ናቸው። ሰዎች የዱንያን ፀጋ አጣጣሙ፣ እነርሱ የአላህን ትዕዛዝ በመፈፀም ተደሰቱ። ሰዎች ፍራሽ እና ወፋፍራም ሴቶች ላይ ተጋደሙ፤ እነርሱ ግን በግንባሮቻቸው እና ጉልበቶቻቸው ለአላህ ተደፉ። ሰዎች የነቢያትን ድርጊቶች እና መልካም ባህሪዎቻቸዉን ተዉ፤ እነርሱ ግን አጥብቀው ያዙ። ምድር እነርሱን ስታጣ ታለቅሳለች። አላህ እነርሱ የሌሉበትን መንደር ሁሉ ይጠላል። ዉሾች ጥንብ ላይ እንደሚረባረቡት ዱንያ ላይ አልተረባረቡም። ከማንኪያ ትራፊ ላሱ፣ አራፊ ጨርቅ ለበሱ፣ የተንጨባረሩና አቧራ የለበሱ ናቸው። ሰዎች ሲያዩዋቸው ታመዋል ብለው ያስባሉ፤ እነርሱ ግን ታመው አይደለም። ይዘባርቃሉ አዕምሯቸዉን የሳቱ ናቸው ይሏቸዋል፣ ግና በአዕምሮ ጤናማ ናቸው። ነገርግን እነርሱ የአላህን ጉዳይ በቀልቦቻቸው ስላዩ የዱንያን ጉዳይ አርግፍ አድርገው ተዉ። እነርሱ በዱንያ ሰዎች ዘንድ አዕምሮ የሌላቸው ተበለው የሚታሰቡ ናቸው። ባይሆን ብዙዎች አዕምሮ በሌላቸው ዘመን እነርሱ ኖራቸው። በመጨረሻው ዓለም ትልቅ ክብር አላቸው። እንዲህ አሉት ለኡሳማ - ኡሳማ ሆይ እነርሱን ያገኘህ እንደሆነ ለአንድ አገር የደህንነት ዋስትና መሆናቸዉን እወቅ። አላህ እነርሱ ያሉበትን አገር ሕዝቦች አይቀጣም። አላህ በነርሱ ተደስቷል፣ ከነርሱም ወዷል። ለራስህ ወንድሞች አድርገህ ያዛቸው። በነርሱ ምክንያት ትድን ይሆናልና። ሆድህ ተርቦ፣ ጉበትህ ተጠምቶ ሞትን ማግኘት ከቻልክ አድርገው። ከዚህ የተነሳ ክብር ታገኛለህ። ከነቢያት ጋር ታርፋለህ። መልአክ ነፍስህን ሊያወጣ ሲመጣ ትደሠታለህ። ጀባር (ጠጋኙ) አላህ እዝነቱን ያወርድብሃል።"

(አል-ኸጢብ አል-በግዳዲ ዘግበዉታል።)

ወዳጆቼ! አላህ የሚወዳቸዉን ሰዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ አስተዋልን አይደል። የቀረን እንደነርሱ ለመሆን መጣር ነው። ለዚህች ዱንያ ዋጋ ሰጥቶ ከርሷ አለመለጠፍ ነው። ይህች ዱንያ ዋጋ የላትም ስላችሁ ወላሂ ዋጋ እንደሌላት ስለማውቅ ነው።